www.abyssinialaw.com


# ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ
## የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ

ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ
የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መበል 14 ዓመት ቑ.5
መቐለ መጋቢት 15/1998 ዓ/ም

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝወፀ

14ኛ ዓመት ቁ. 5
መቐለ መጋቢት 15/1998 ዓ/ም


### ኣዋጅ ቁፅሪ 98/1998 ዓ.ም
### መማሓየሺ ሕገ-መንግስቲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ መፅደቒ ኣዋጅ ቁፅሪ 45/1994 ዓ.ም ንምምሕያሽ ዝወፀ ኣዋጅ

ተመሓይሹ ዝወፀ ሕገ-መንግስቲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ንምምሕያሽ ኣድላዪ ኮይኑ ስለዝተረኸበ፣ ብመሰረት ዓንቀፅ 107(2) ተመሓይሹ ዝወፀ ሕገ-መንግስቲ ዝስዕብ መመሓየሺ ኣዋጅ ወፂኡ ኣሎ፡፡

1. **ሓፂር ርእሲ**

እዚ ኣዋጅ "መፅደቒ ዝተመሓየሸ ሕገ-መንግስቲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ኣዋጅ ቁፅሪ 45/1994 ንምምሕያሽ ዝወፀ ኣዋጅ ቁፅሪ 98/1998" ተባሂሉ ክጥቀስ ይኽእል፡፡

2. **መመሓየሺ**

1. ዓንቀፅ 52 ንኡስ ዓንቀፅ (3) ናይቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡

3. ካብ ኣባላት እቲ ቤት ምኽሪ ልዕሊ ፍርቂ (50%+1) እንተተረኺቦም ምልኣተ ጉባኤ ይኸውን፣ ውሳነ እቲ ቤት ምኽሪ ኣብዚ ሕገ-መንግስቲ ብፍሉይ ኹነታት እንተዘይተደንጊጉ ኣብቲ ኣኼባ ካብ ዝተረኸቡ ኣባላት ልዕሊ ፍርቂ እንትድግፍዎ ይመሓላለፍ፡፡

### አዋጅ ቁጥር 98/1998 ዓ.ም
### ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት ማጽደቅያ አዋጅ ቁጥር 45/1994 ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ተሻሽሎ የወጣው የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ ተሻሽሎ በወጣው ሕገ-መንግስት አንቀጽ 107(2) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ "ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ማጽደቅያ አዋጅ ቁጥር 45/1994 ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 98./1998" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

1. የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 52 ንኡስ አንቀጽ(3) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

3. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ (50%+1) ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፣ በዚህ ህገ-መንግስት በሌላ አኳሃን ካልተደነገገ በስተቀር የምክር ቤቱ ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ ከተገኙ አባላት ከግማሽ በላይ ሲደግፉት ይሆናል ፡፡


ናይ ሓደ ዋጋ
ያንዱ ዋጋ
ብር 1.90

ነጋሪት ጋዜጣ ቑ.ፖ.ሳ
ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሳ.ቁ

www.abyssinialaw.com





2. ዓንቀፅ 59 ንኡስ ዓንቀፅ (1) ናይቲ ሕገ -መንግስቲ መእተዊ ክፋሉ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡

1. ምክትል ርእሰ ምምሕድዳር ካብ መንጎ ኣባላት ቤት ምኽሪ እዚ ክልል ወይ ድማ ካብ ኣባላት ቤት ምኽሪ ወፃኢ ብመቕረባይነት ርእሰ ምምሕድዳር ብቤት ምኽሪ ዝሽወም ኮይኑ፣

3. ኣብ ዓንቀፅ 73 እቲ ሕገ-መንግስቲ ዝስዕቡ ሓደሽቲ ንኡሳን ዓንቀፃት 3፣ 4፣ 5፣6ን 7ን ተወሲኾም ኣለዉ፡፡

3. ተፀዋዕነት ቤት ምኽሪ ወረዳ ንቤት ምኽሪ ክልል ትግራይን ንነበርቲ እቲ ወረዳን ይኾውን፣

4. ሕገ-መንግስታዊ ስርዓት ኣብ ሓደጋ ዘውድቕ ተግባር እንትፍፀም ወይ እቲ ወረዳ ምምሕድዳር ፀጥታን ድሕንነትን እቲ ከባቢ ምቁፅፃር እንትኣብዮ ወይ ከዓ ብሕጊ ዝተውሃቦ ስልጣንን ተግባርን ብኣግባቡ ክዋፃእ ኣይከኣለን ኢሉ እንትውስን፣

ሀ. ቤት ምኽሪ ክልል ትግራይ ናይቲ ወረዳ ቤት ምኽሪ ወይ ስራሕ ፈፃሚ ከፍርስ፣ ናይ ስግግር ምምሕድዳር እቲ ወረዳ ብምጥያሽ እቲ ስግግር ዝፀንሓሉ እዋን ይውስን፣

ለ. እቲ ወረዳ ኣብ ከምዚ ዝበለ ኩነታት እናሃለወ ኣብ ጣብያ ቤት ምኽሪ ፀገም እንተተፈጢሩ ቤት ምኽሪ ክልል ትግራይ ከፍርስን መሰጋገሪ ምምሕዳር ንክጣየሽ ይውስን፡፡

ሐ. ርእሰ ምምሕዳር እዚ ክልል ውሳኔታት እቲ ቤት ምኽሪ የተግብር፣ ናይቲ ወረዳ ናይ ስግግር ምምሕድዳር ይውድብ፣ ሓለፍቲ ግዚያዊ ምምሕድዳር ይምደብ፣ እቲ ስግግር ብመሰረት ውሳነ ቤት ምኽሪ ክልል ተግባራዊ ምዃኑ የረጋግፅ፣

መ. ኣብ ምፍራስ ቤት ምኽሪ ወይ ስራሕ ፈፃሚ ወረዳ ኣብ ዝከኣለሉ እዋን ምስ መራፂ ህዝቢ እቲ ወረዳ ምኽክር ክግበር ቤት ምኽሪ እዚ ክልል ክውስን ይኽእል፡፡

2. የሕገ-መንግስቱ ዓንቀፅ 59 ንኡስ ዓንቀፅ (1) መግቢያው ክፍል እንደሚከተው ተሻሽሏል፣

1. ምክትል ርእሰ መስተዳድሩ ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል ወይም ምክር ቤቱ ከአባላት ውጭ በርእሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚሾም ሆኖ፣

3. በሕገ- መንግስቱ አንቀጽ 73 የሚከተሉት አዳዲስ ንኡስ አንቀጾች 3፣ 4፣ 5፣ 6 እና 7 ተጨምረዋል፡፡

3. የወረዳ ምክር ቤት ተጠሪነት ለክልሉ ምክር ቤትና ለወረዳው ነዋሪዎች ይሆናል፡፡

4. ሕገ - መንግስታዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር ሲፈጽም ወይም የወረዳው አስተዳደር የአከባቢውን ፀጥታና ደሕንነት መቆጣጠር ሲያቅተው ወይም በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ሊተገብር አልቻለም ብሎ ሲወስን፣

ሀ. የትግራይ ክልል ምክር ቤት የወረዳው ምክር ቤት ወይም ስራ አስፈጻሚው አካል ማፍረስ፣ የሽግግር አስተዳደር በማቋቋም የሽግግሩ ወቅት የሚቆይበት ጊዜ ይወስናል፡፡

ለ. ወረዳው በዚህ ሁኔታ እያለ በቀበሌ ምክር ቤት ችግር ከተፈጠረ የትግራይ ክልል ምክር ቤት እንዲፈርስ እና የሽግግር አስተዳደር እንዲቋቋም ይወስናል፡፡

ሐ. የክልሉ ርእሰ መስተዳድር የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ይተገብራል፣ የወረዳውን የሽግግር አስተዳደር ያደራጃል፣ የአስተዳደሩ ግዚያዊ ሓላፊዎችን ይመድባል፣ ሽግግሩ በክልሉ ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

መ. የወረዳው ምክር ቤት ወይም ስራሕ አስፈጻሚው በሚፈርስበት ወቅት አመቺ በሆነ ወቅት ከመራጩ የወረዳው ህዝብ ምክክር እንዲደረግ የክልሉ ምክር ቤት ሊወስን ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com



5. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 4 (ሀ)ን (ለ)ን ዝጣየሽ ናይ ስግግር ምምሕድዳር ዝስዕቡ ስልጣንን ተግባርን ይህልዉዎ፣
   ሀ. ብመሰረት ሕገ-መንግስቲ ዓንቀፅ 80ን 82ን ንወረዳ ኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕን ዋና ኣመሓዳርን ዝተውሃቡ ስልጣንን ተግባርን ይፍፅም፣ የፈፅም፣
   ለ. ናይቲ ወረዳ ትልምን በጀትን የፅድቕ፣ የፈፅም፣
   ሐ. ኣግባብ ብዘለዎ ሕጊ መሰረት ኣብቲ ወረዳ መረፃ ዝካየደሉ ኩነታት የመቻቹ፣
   መ. ብክልል ቤት ምኽሪ ስራሕ ፈፃሚ ዝወሃብዎ ካልኦት ተግባራት ይፍፅም፣
6. እቲ ግዚያዊ ናይ ስግግር ምምሕድዳር ዝፀንሓሉ እዋን ካብ ሓደ ዓመት ንዘይበልፅ ይኸውን፡፡ ኮይኑ ግና እድላይ ኮይኑ እንትርከብ ቤት ምኽሪ ክልል ትግራይ እዚ መፅንሒ እዋን ካብ ሽድሽተ (6) ወርሒ ንዘይበልፅ እዋን ክናውሖ ይኽእል፡፡ ኣብዚ ግዚ ብመሰረት ሕጊ ዳግም መረፃ ተኻይዱ ስሩዕ ምምሕድዳር ይጣየሽ፣
7. ኣብ እዋን እቲ ስግግር ተሳትፎ ነበርቲ ህዝቢ እቲ ወረዳ ኣብ ልምዓት፣ ሰናይ ምሕድዳርን ህንፀት ዲሞክራሲ ከምኡ'ውን ቀረብ ግልጋሎት ብዝተወደበ መልክዑ ንምትልባትን ናይቲ ህዝቢ ጥቅምታት ዝሕልዉ ውሳነታት ንምውሳን ካብ ነበርቲ እቲ ወረዳን ዝተፈላለዩ ክፋላት ሕብረተሰብን ዝተወከሉ ዝካፈልሉ ኣማኻሪ ኣብያተ ምኽርታት ኣብ ብርኪ ወረዳን ጣብያን የጣይሽ፣ ዝርዝሩ በቲ ግዚያዊ ምምሕድዳር ይውሰን፣
4. ናይቲ ሕገ-መንግስቲ ዓንቀፅ 74 ንኡስ ዓንቀፅ 2(ቀ) ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡
   ቀ. ንሕገ - መንግስታትን ካልኦት ሕግታትን ፌደራልን ክልልን ዘይፃባእን በዞም ሕግታት ዘይተሸፈኑ፣ ንምርግጋፅ ሰላምን ፀጥታን እቲ ወረዳ ዝሕግዙ፣ ንናይቲ ወረዳ ፍሉይ ኩነታትን ባህርን ዝምልከቱ ኣብ ወረድኡ ጥራሕ ዝፍፀሙ ናይ ግልጋሎትን ሚሕበራዊ ጉዳያትን ዝርዝር መምርሕታት ኣውፂኡ ኣብ ስራሕ የውዕል፡፡



5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4(ሀ) እና (ለ) መሰረት የሚቋቋም የሽግግር አስተዳደር የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣
   ሀ. በሕገ-መንግስቱ ዓንቀፅ 80 እና 82 ለወረዳው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ለዋና አስተዳዳሪው የተሰጠ ስልጣንና ተግባር ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣
   ለ. የወረዳው ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፣ ያስፈፅማል፣
   ሐ. አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የወረዳው ምርጫ የሚካሄድበት ሁኔታ ያመቻቻል፣
   መ. በክልሉ ስራ አስፈጻሚ ምክር ቤት የሚሰጡት ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል፣
6. ጊዚያዊው የሽግግሩ አስተዳደር የሚቆየው ከአንድ አመት ላልበለጠ ግዜ ይሆናል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የክልሉ ምክር ቤት የመቆያ ጊዜው ከስድስት (6) ወር ላልበለጠ ጊዜ ማራዘም ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ በሕግ መሰረት ምርጫ ተካሂዶ መደበኛው አስተዳደር ይቋቋማል፣
7. በሽግግሩ ወቅት በልማት፣ መልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ግንባታ እንዲሁም በአገልግሎት አቅርቦት የወረዳው ነዋሪ ህዝብ የተደራጀ ተሳትፎ ለማጎልበትና የህዝቡን ጥቅም የሚያስጠብቅ ውሳኔዎች ለመወሰን እንዲቻል ከወረዳው ነዋሪዎችና ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተወከሉ የሚሳተፉበት አማካሪ ምክር ቤቶች በወረዳ እና ቀበሌ ደረጃ ያቋቁማል ዝርዝሩ በግዚያዊ አስተዳደሩ ይወሰናል፡፡
4. የሕገ- መንግስቱ አንቀጽ 74 ንኡስ አንቀጽ 2(ቀ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡
   ቀ. የፌደራልና ክልል ሕግጋተ መንግስትና ሌሎች ሕጎችን የማይቃረኑና በነዚህ ሕጎች ያልተሸፈኑ፣ ለወረዳው ሰላምና ፀጥታ መረጋገጥ የሚያግዙ፣ የወረዳውን ልዩ ሁኔታና ባህሪ የሚመለከቱ በወረዳው ብቻ የሚፈጸሙ የአገልግሎትና ማሕበራዊ ጉዳዮች ዝርዝር መመሪያዎች አውጥቶ ስራ ላይ ያውላል፡፡

www.abyssinialaw.com





በ. በቤት ምኽሪ ክልል ትግራይ ብዘውፅእ ኣዋጅ መሰረት መምርሕታት ከውፅእ ስልጣን እንትውሃቦ ኣውፅኡ ኣብ ስራሕ የውዕል፡፡

ተ. ንዋና ኣማሓዳርን ካልኦት ሓለፍቲ እቲ ወረዳ ንሕቶ ይፅውፅ፡፡ ስራሕቶም ይምርምር፡፡

5. ዓንቀፅ 77 ንኡስ ዓንቀፅ (3) እቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡

3. ካብ ኣባላት ቤት ምኽሪ እቲ ወረዳ ልዕሊ ፍርቂ (50%+1) እንተተረኺቦም ምልኣተ ጉባኤ ይኾውን፡ ውሳነ እቲ ቤት ምኽሪ ኣብቲ ቤት ምኽሪ ካብ ዝተረኽቡ ኣባላት ብልዕሊ ፍርቂ (50%+1) ድምፂ እንተተደጊፉ ይመሓላለፍ፡፡

6. ዓንቀፅ 78 እቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ይመሓየሽ፡፡

ቤት ምኽሪ ወረዳ ናይ ባዕሉ ቤት ፅሕፈት ይህልዎ፡ እቲ ቤት ፅሕፈት ክሳብ ዝጣየሽ ግን ቤት ፅሕፈት ፈፃሚት እቲ ወረዳ ቤት ፅሕፈት ኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕን ቤት ምኽሪ እቲ ወረዳ ብትሕዝቶኦም ከይተሓዋወሱ ብሓባር ስርሖም ዘካይድሉ ቤት ፅሕፈት ኮይኑ የገልግል፡፡

7. ኣብ ዓንቀፅ 82 እቲ ሕገ-መንግስቲ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ (3) ተወሲኹ ኣሎ፡፡

3. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) ዋና ኣመሓዳሪ ወረዳ ንርእሰ ምምሕድዳር እዚ ክልል ተፀዋዒ ዝኾነሉ መዳያትን ኣገባባትን ብሕጊ ይውሰን፡፡

8. ዓንቀፅ 83 ንኡስ ዓንቀፅ (1) እቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡

1. ምክትል ዋና ኣማሓዳሪ ወረዳ ካብ መንጎ ኣባላት ቤት ምኽሪ እቲ ወረዳ ወይ ካብ ኣባላት ቤት ምኽሪ ወፃኢ ብመቕረባይነት ዋና ኣማሓዳሪ ወረዳ ብቤት ምኽሪ ወረዳ ይሽመም፡፡

9. ዓንቀፅ 85 ንኡስ ዓንቀፅ (1) እቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡

1. ምምሕድዳር ጣብያ ናይቲ ክልል ታሕተዋይን ናይ መወዳእታን ብርኪ መንግስታዊ መሓውር እዩ፡፡

በ. የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው አዋጅ መሰረት መመሪያዎች እንዲያወጣ ስልጣን ሲሰጠው አውጥቶ ስራ ላይ ያውላል፡፡

ተ. ዋና አስተዳዳሪውንና ሌሎች የወረዳ ስራ ሃላፊዎችን ለጥያቄ ይጠራል፡፡ ስራዎቻቸውን ይመረምራል፡፡

5. የሕገ - መንግስቱ አንቀጽ 77 ንኡስ አንቀጽ (3) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

3. ከወረዳው ምክር ቤት አባላት ከግማሽ በላይ (50%+1) ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ ከተገኙ አባላት ከግማሽ በላይ ሲደግፉት ይሆናል፡፡

6. የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 78 እንደሚከተለው ተሻሽሏልሽ፡፡

የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ፅህፈት ቤት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ምክር ቤቱ የራሱ ፅህፈት ቤት እስኪያደራጅ ድረስ የስራ አስፈፃሚው ምክር ቤት የስራ ድርሻ ሳይቀላቀል የወረዳው ስራ አስፈፃሚ ፅህፈት ቤት በጋራ ስራዎቻቸው የሚያካሄዱበት ፅህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

7. በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 82 የሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ 3 ተጨምሯዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ለክልሉ ርእሰ መስተዳድር ተጠሪ የሚሆንበት ሁኔታና አገባብ በሕግ ይወሰናል፡፡

8. የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 83 ንኡስ አንቀጽ (1) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1፡ የወረዳው ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ከወረዳው ምክር ቤት አባላት ወይም ከምክር ቤቱ አባላት ውጭ በዋና አስተዳዳሪው አቅራቢነት በወረዳው ምክር ቤት ይሾማል፡፡

9. የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 85 ንኡስ አንቅጽ (1) እንደሚተለው ተሻሽሏል፡፡

1. የቀበሌው አስተዳደር የክልሉ ዝቅተኛውና የመጨረሻው መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡

www.abyssinialaw.com





10. ዓንቀፅ 86 ንኡስ ዓንቀፅ (4) እቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡
ቤት ምኽሪ ጣብያ ተፀዋዕነቱ ንዝመረፆ ህዝብን ከከምኩነታቱ ንቤት ምኽሪ ወረዳ ወይ ቤት ምኽሪ ከተማ ይኸውን፡፡

11. ኣብ ዓንቀፅ 86 እቲ ሕገ - መንግስቲ ዝስዕቡ ሓደሽቲ ንኡስ ዓንቀፃት 5፡ 6፡ 7ን 8ን ተወሲኾም ኣለዉ፡፡

5. ሕገ-መንግስታዊ ስርዓት ኣብ ሓደጋ ዘውድቕ ተግባር በቲ ጣብያ እንትፍፀም ወይ እቲ ጣብያ ምምሕድዳር ፀጥታን ደሕንነትን ከባቢኡ ምቁፅፃር ኣንትኣብዮ ወይ እቲ ጣብያ ብሕጊ ዮተውሃቦ ስልጣንን ተግባርን ብኣግባቡ ክዋፃእ ኣይከኣለን ኢሉ እንትውሰን፡

ሀ. ቤት ምኽሪ ወረዳ ናይቲ ጣብያ ቤት ምኽርን ወይ ስራሕ ፈፃሚ ክፍርስ፣ ናይቲ ጣብያ ስግግር ምምሕድዳር ክጣይሽን እቲ ስግግር ዝፀንሓሉ እዋን ክውሰን ይኽእል፣

ለ. ዋና ኣመሓዳሪ ወረዳ ኣብ ስልጣን ዘሎ ምምሕድዳር ጣብያ የሰናብት፣ ናይቲ ጣብያ ናይ ስግግር ምምሕድዳር ይውድብ፣ ግዚያዊ ሓለፍቲ ምምሕድዳር ይምድብ፣ እቲ ስግግር ብመሰረት ውሳነ ቤት ምኽሪ ወረዳ ተግባራዊ ምኻኑ የረጋግፅ፣

ሐ. ኣብ ምፍራስ ቤት ምኽሪ ወይ ስራሕ ፈፃሚ ጣብያ ኣብ ዝከኣለሉ እዋን ቤት ምኽሪ ወረዳ ነቲ ጣብያ መራፂ ህዝቢ የማኽር፣

6. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 5 (ሀ)ን (ለ)ን ዝጣየሽ ናይ ስግግር ምምሕድዳር ብመሰረት እዚ ሕገ-መንግስቲ ዓንቀፅ 91 ን 93 ን ንኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕን ኣመሓዳሪ ጣብያን ተውሂቦ ስልጣንን ተግባርን ይፍፅም፣ የፈፅም፣

10. የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 86 ንኡስ አንቀፅ (4) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡
የቀበሌ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለመረጠው ህዝብና እንደየሁኔታው ለወረዳው ወይም ከተማ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

11. በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 86 የሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀፆች 5፣6፣ 7 እና 8 ተጨምሯል፡፡

5. ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር ሲፈጽም ወይም የቀበሌው አስተዳደር የአከባቢውን ፀጥታና ድሕንነት መቆጣጠር ሲያቅተው ወይም በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ሊተገብር አልቻለም ብሎ ሲወሰን፣

ሀ. የወረዳው ምክር ቤት የቀበሌውን ምክር ቤት ወይም ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ማፍረስ፣ የሽግግር አስተዳደር ማቋቋምና የሽግግሩ ወቅት የሚቆይበት ግዝ መወሰን ይችላል፡፡

ለ. የወረዳው ዋና አስተዳደሪ በስልጣን ላይ ያለውን አስተዳደር ያሰናብታል፣ የወረዳው የሽግግር አስተዳደር ያደረጃል፣ የአስተዳደሩ ጊዚያዊ ሓላፊዎችን ይመድባል፣ ሽግግሩ በወረዳው ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

ሐ. የቀበሌው ምክር ቤት ወይም ስራ አስፈጻሚው ለማፍረስ በሚወሰንበት ጊዜ የወረዳው ምክር ቤት አመቺ በሆነበት ወቅት መራጩ የቀበሌው ህዝብ ያማክራል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 (ሀ) እና (ለ) መሰረት የሚቋቋም የሽግግር አስተዳደር በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 91 እና 93 መሰረት ለቀበሌው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና አስተዳዳሪው የተሰጠውን ስልጣን ተግባር ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

www.abyssinialaw.com



7. ግዚያዊ ናይ ስግግር ምምሕድዳር ጣብያ ዝፀንሓሉ እዋን ካብ ሽዱሽተ ወርሒ ዘይበልፅ ይኸውን፡፡ ኾይኑ ግን እንትርከብ ቤት ምኽሪ ወረዳ እዚ እዋን ካብ ሽዱሽተ ወርሒ ንዘይበልፅ ከናውሖ ይኽእል፡፡ ኣብዚ ግዘ ኣግባብ ብዘለዎ ሕጊ መሰረት ዳግም መረፃ ተኻይዱ ስሩዕ ምምሕድዳር ይጣየሽ፡፡

8. ኣብ እዋን ስግግር ናይቲ ህዝቢ ዝተወደበ ተሳትፎ ንምጥንኻር ካብ ዝተፈላለዩ ክፋላት ሕብረተሰብ ዝተውፃዕኡ ኣባላት ዝሓዘ መማኽሪ ቤት ምኽሪ ይጣየሽ፡ ዝርዝሩ በቲ ወረዳ ቤት ምኽሪ ይውሰን፡፡

12. ዓንቀፅ 89 ንኡስ ዓንቀፅ (2) ናይቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡

   2. ካብ ኣባላት ቤት ምኽሪ ጣብያ ልዕሊ ፍርቂ (50%+1) እንተተረኺቦም ምልኣተ ጉባኤ ይኸውን፡፡ ውሳነ እቲ ቤት ምኽሪ ኣብቲ ኣኼባ ካብዝተረኸቡ ኣባላት ብልዕሊ ፍርቂ (50%+1) እንተተደጊፉ ይመሓላለፍ፡፡

13. መእተዊ ክፍሊ ዓንቀፅ 94 እቲ ሕገ-መንግስቲ ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ፡፡ ምክትል ኣመሓዳሪ ጣብያ ካብ መንጎ ኣባላት ቤት ምኽሪ ጣብያ ወይ ካብ ኣባላት ቤት ምኽሪ ወፃኢ ብመቕረባይነት ኣመሓዳሪ ጣብያ ዝሸየምን ተፀዋዕነቱ ንኣማሓዳሪ ጣብያ ኮይኑ፣

## 3. እዚ ኣዋጅ ዝፀንዐሉ እዋን

እዚ ኣዋጅ ካብ መጋቢት 15/1998 ዓ/ም ጀሚሩ ዝፀንዐ ይኸውን፡፡

ፀጋይ በርሀ

ፕሬዚዳንት

ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ



7. ግዚያዊ የሽግግሩ አስተዳደር የሚቆይበት ጊዜ ከስድስት ወር ላልበለጠ ግዘ ይሆናል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የወረዳው ምክር ቤት የመቆያ ጊዜው ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊቴ ሊያራዝመው ይችላል፡፡ በዚሁ ጊዜ አግገብ ባለው ሕግ መሰረት ምርጫ ተካሂዶ መደበኛው አስተዳደር ይቋቋማል፡፡

8. በሽግግሩ ወቅት የህዝቡን የተደረጀ ተሳትፎ ለማጠናከር ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ አባላት የያዘ አማካሪ ምክር ቤት ያቋቁማል፣ ዝርዝሩ በወረዳው ምክር ቤት ይወሰናል፡፡

12. የሕገ- መንግስቱ አንቀጽ 89 ንኡስ አንቀጽ 2 እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፡፡

   2. ከቀበሌው ምክርቤት አባላት ከግማሽ በላይ (50%+1) ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ ከተገኙ አባላት ከግማሽ በላይ (50% + 1) ሲደግፉት ይሆናል፡፡

13. የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 94 የመግቢያው ክፍል እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡ የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ወይም ከምክር ቤቱ አባላት ውጭ በቀበሌው አስተዳዳሪ አቅራቢነት የሚሾምና ተጠሪነቱም ለቀበሌው አስተዳዳሪ ሆኖ፣

## 3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 15/1998 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ፀጋይ በርሀ

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዚዴንት